# የሥነ - ጥበባት ትምህርት
# የተማሪው መጽሐፍ
## 2ኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ደሜ ቶሊና

ሉባባ ጀማል

ታደሰ ድንቁ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ደንደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዩ

እስማኤል ሐሰን

**ተርጓሚ**

በርናባስ ደበሎ

**ኤዲተር**

ደቀቦ ጉዩ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡ ፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝቶ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መዉጫ

ምዕራፍ 1: የስነጥበብ ግንዛቤ........................................................................1

1.1 የሙዚቃ ኖታዎች ...........................................................................1

1.3. የቀላል ተውኔት ጨዋታ......................................................................10

1.4 የፎቶ ምልከታ..............................................................................22

1.5 የተለያዩ ተግባራት ...........................................................................26

ምዕራፍ 2: የፈጠራ ችሎታ ..........................................................................30

2.1የሙዚቃ ኖታዎችን የመጻፍ፣ የማንበብና ..................................................30

የመጫወት ፈጠራ ችሎታ ......................................................................30

2.2 ውዝዋዜ እና ነጻ እንቅስቃሴ ................................................................34

2.3 የተውኔት ጨዋታ ፈጠራ.....................................................................37

2.4 መስመሮችን ማስመር እና መንደፍ .........................................................42

ምዕራፍ 3: የታሪክ እና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ .................................................53

3.1 የባህል ሙዚቃ እና ውዝዋዜ .................................................................53

3.2 ተረት.........................................................................................58

3.3 ባህልን የሚገልጽ ቀለም ......................................................................67

3.4 ባህላዊ ድራማ ..............................................................................74

ምዕራፍ 4: የስነጥበባት ማራኪነት በባት ......................................................80

4.1 ሙዚቃ ሳቢኔት ማድነቅ......................................................................80

4.2. የስነጥበባትን ስራዎች ማድነቅ ..........................................................81

4.3 የተውኔት ጨዋታ ....................................................93

ምዕራፍ 5: የስለጥበባት ግንኙነት ....................................................98

5.1 የሙዚቃ ተግባራት ....................................................98

5.2 በስነጥበባት መካከል ያለ ግንኙነት ....................................100

5.3 የስነጥበባት ዕውቀት ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ያለቸው አስፈላጊነት ....................................................102

5. 3. 2· ሙዚቃን በተመለከተ ............................................108

5. 3. 3. ስነጥበብን በተመለከተ ............................................109

# ምዕራፍ 1
# የስነጥበብ ግንዛቤ

## 1.1 የሙዚቃ ኖታዎች

### የኖታ መዝሙር



ኖታ የሙዚቃ ፍደል ነው
እሱም የተለየ ፈጠራ ነው
የተለያዩ ኖታዎች አሉ
የራሱ የሆኔ ሳይንስም አለው 2x

ኖታ የሙዚቃ ፊደል ዜማ እና ምትን ጠብቆ የሚጻፍበት ነው።

ሀ. ዜማ ድምጽ ለሰዎች ጆሮ በሚመች ሁኔታ ፍሰቱን ጠብቆ የሚዘመር ነው።

ለ. ምት ደግሞ ከሙዚቃ ክፍሎች መካከል የሙዚቃ ልብ ተብሎ የሚታወቅ ነው።

የተለያዩ የሙዚቃ ኖታዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ:-

## 1. ሙሉ ኖታ እና ሙሉ ዕረፍት

ሀ. ሙሉ ኖታ

ሙሉ ኖታ ክብ ቅርጽ አለው። የምቱም ዋጋ አራት ነው ።

የሙሉ ኖታ ቅርጽ የሚከተለውን ይመስላል።

O = 4

ተግባር

ከዚህ በታች ያሉትን ሙሉ ኖታዎች ድምጻችሁን ሳታቋርጡ ታ· ··ታ በማለት አራት ጊዜ እያጨበጨባችሁ በመቁጠር እያነበባችኋቸሁ ተጫወቱ።




ለ. ሙሉ ዕረፍት

ሙሉ ዕረፍት እንደ ሙሉ ኖታ ሁሉ አራት ምቶች አሉት። ነገር ግን ተጫዋቾች ጨዋታውን ምንም ድምጽ

ሳያሰሙ በጸጥታ ነው የሚጫወቱት::

የሙሉ ዕረፍት ቅርጽ


 =4

ሙሉ ዕረፍት አራት የምት ቆይታ ጊዜ አለው::

ጨዋታው ድምጽ የለውም በፀጥታ ነው የሚከናወነው::

## ልምምድ



1. 

1. 


2. 

## 2. ግማሽ ኖታና ግማሽ ዕረፍት

### ሀ. ግማሽ ኖታ

ግማሽ ኖታ ድምፅና ሁለት የምት ቆይታ ጊዜ አለው:: ጨዋታው ታ… እያሉ በማጨብጨብ ነው የሚከናወነው::


የግማሽ ኖታ ቅርጽ




**ግንድና ራስ ቦታው ይቀያየር**

**ልምምድ**


ግማሽ ኖታን እያነበቡ መጫወት





1.

ታ ታ ታ

2.



3.






4.



## ለ. ግማሽ ዕረፍት


ግማሽ ዕረፍት እንደ ሙሉ ዕረፍት ድምፅ የሌለውና ሁለት የምት ቆይታ ያለው ነው:: ይህ ጨዋታም በጸጥታ ነው የሚከናወነው::

የግማሽ ዕረፍት ቅርጽ



# ልምምድ




1. 

2. 

3. 

## የግማሽ ኖታ እና የግማሽ ዕረፍት ዋጋ እኩል ነው::



2 = 2

ድምጽ አለሁ          ድምጽ የለውም

## ግማሽ ኖታ ስር ድምጽ አለው በሚል ይስተካከል

## ልምምድ

**በእጃችን እያጨበጨብን ድምጽ እያሰማን "ታ" በማለትና ደግሞም በጸጥታ የሙዚቃ ኖታን እያነበቡ መጫወት::**

1. 

2. 

3. 

4. 

## 1.2. ወዝዋዜና ዳንስ

### መሰረታዊ የውዝዋዜና የዳንስ አስተሳሰብ

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ውዝዋዜ ምንድን ነው ?
2. ሰዎች እንዴት ነው ውዝዋዜን የሚያደርገት ?

ውዝዋዜ የሙዚቃ ምትን ተከትሎ የሚካሄድ የአካል እንቅስቃሴ ነው።ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ከግዜ ወደ ግዜ እየተሻሻለ የመጣ ነው።

ውዝዋዜ ባህላዊና ዘመናዊ በመባል በሁለት ይከፈላል።

ሀ. ባህላዊ ውዝዋዜ በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ቅንብር ይቀርብ የነበረና ያለ ነው።

ለ. ዘመናዊ ውዝዋዜ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ተቀናብሮ የሚቀርብ ጭፈራ ነው።

ዳንስ ደግሞ ሰዎች ስርአት ባለው መንገድ የሚከውኑት ሳይሆን እንደተመቻቸውና እንደ ቻሉት የሙዚቃን ምት ሂደት በመከተልና ሰውነታቸውን በማንቀሳቀስ የሚያከናውኑት የጭፈራ አይነት ነው።

## 1.3. የቀላል ተውኔት ጨዋታ

የተውኔት ጨዋታ ከስነጥበብ ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው:: የተውኔት ጨዋታ በአንድ ሰው ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በመድረክ ላይ ወይም በተመልካቾች ፊት በተግባር የሚቀርብ ነው::

### 1.3.1. የተውኔት ጨዋታ ጥቅም

የአንድን ታሪክ ጽሑፍ ሙሉ ለማድረግ ሰዎች በሚያደርጓቸው ልምምዶች ውስጥ የሚከተሉትን ጥቅሞች ሊያገኙ ይችላሉ::

ሀ. የመተንተን/የመመራመር ችሎታ ያዳብራሉ::
ለ. የቃላትን ቅደም ተከተላዊ አገባብ ይገነዘባሉ::
ሐ. የማስታወስ ችሎታቸውን ያደብራሉ::
መ. በራስ መተማመንን ያጎለብታሉ::
ሠ. ፊትለፊት በመውጣት ያለምንም ፍርሀት ንግግር እንድያደርጉ ይረዳቸዋል::

#### የግንዛቤ ጥያቄ

ቀጥሎ የቀረበውን ጥያቄ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሁፍ መልሱ::

1. ተውኔት ከስነጥበብ አይነቶች መካከል አንዱ ነው::

#### የግንዛቤ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረበ ጥያቄ ከስሩ ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::

1. ከሚከተሉት የተውኔት ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. በራስ መተማመንን ለማጎልበት
   ለ. በሰው ፊት በመውጣት ምንም ሳይፈሩ መናገር መቻል
   ሐ. አንድን ነገር የመመራመር ችሎታ ማዳበር
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## የአውራ ዶሮ ጉድ


ይህ የተውኔት ጨዋታ በሁለት ወንድማማቾች ሕይወት ታሪክ ላይ የሚያተኩር ነው።




ይህንን ጨዋታ ለመጫወት ከመምህራችሁ ጋር ክብ ሰርታችሁ ተጫወቱ።

ማሳሰቢያ፡ ከቁጥሮች ጋር የተሰጡ ፊደላት ተማሪዎችን የሚወክሉ ናቸው። ይህም 1 ቁጥር ያለው ፊደል አንደኛ

የሚናገር ተማሪ፣ 2 ቁጥር ያለው ፊደል ሁለተኛ የሚናገር ተማሪ........ወዘተ ይወክላል።











መምህርት
አባታቸሁ በሞት ከዚህ ዓለም ተለዩአቸው::
ሕ 2: ሕጻናቱም የአባታቸውን ንብረት ተከፋፈሉ::
ሕ2
ሕ3
ታላቁ ወንድማቸሁ ሁሉንም የአባታቸውን ንብረት ለራሱ ወስዶ ለታናሽ ወንድሙ አንድ አውራ ዶሮ ብቻ ሰጠው::
ታላቅ ወንድማቸው ታመመ::
መምህርት
ሕ4
ባለመድሀኒት አዋቂ ጋ ሄደ


ሕ5
አዛውንቱም አውራ ዶሮ
አርደ ብላ አለው::
እሱም የወንድሜን አውራ
ዶሮ እረዱልኝ አለ::
ሕ6
መምህርት
ሕ7:የወንድሙ ዶሮ ታረደለት
ነገር ግን አልተሻለውም::
ልክ ነው:: የራሴን ቆጥቤ
የወንድሜን ነበር ያረድኩት
መምህርት
ሕ9
ሕ8
ሕ7
ሕ6
መምህርት
አዛውንቱም ንብረቱን መልስለት
አለሁ::
ሕ9
ሕ8
ሕ7
ሕ6




## መልመጃ 2

1. የዚህ ተውኔት ጨዋታ መልዕክት ምንድን ነው?
2. በዚህ ጨዋታ ውስጥ ምን አስደሰታችሁ?


# 1.4. የተለያዩ ክስተቶች ስዕል

## ተግባር 1

1. በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የቤት እንስሳት፣ የዱር አራዊት፣ ወፎች እና እጽዋት ምን ምን ናቸው? ለመምህራችሁ ተናገሩ::
2. ከተመለከታችሁት ውስጥ በጣም ያስደነቃችሁ የትኛው ነው? ለምን እንደተደነቃችሁበት ለመምህራችሁ ተናገሩ::

## የቤት እንስሳት ስዕል


የቤት እንስሳት ማለት በሰው ልጆች ተላምደው ከሰው ጋር የሚኖሩ ማለት ነው::




ስዕል 1: የቤትእንስሳትን የሚያሳይ ስዕ

## የዱር አራዊት ስዕል


የዱር አራዊት ማለት ከሰው ልጆች ጋር ሳይላመዱ በዱር ወይም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ማለት ነው::



አንበሳ



ነብር



የሜዳ አህያ



ቀጭኔ


ቀይ ቀበሮ


ዝሆን



ጉማሬ


ሚዳቆ


ጅብ

የዱር እንስሳትን የሚያሳይ ስዕል

# የወፎች ስዕል




የወፎችን ስዕል የሚያሳይ

# የተክሎች ስዕል


ኦዳ


ዝግባ


ዋንዛ


ወይራ


ወሌንሱ


ግራር


ጽድ


ኮሶ

*ዕጽዋትን የሚያሳይ ስዕል*

| | | |
|---|---|---|
| <br>ጋሪ | <br>አህያ | <br>ግመል |
| <br>ሳይክል | <br>ሞተር ሳይክል | <br>ባጃጅ |
| <br>መኪና | <br>ባቡር | <br>አውሮፕላን |

ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎችን የሚያሳይ

# የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች ስዕል



ምግብ



ቤት



ልብስ

## 1.5 የየእለት ተግባራት

### ተግባር 2

በአከባቢያችሁ የሚገኙ ሰዎች በየዕለቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው? እናንተ ጠዋት ከእንቅልፋችሁ ከተነሳችሁ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳችሁ በፊት ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ?

በየዕለቱ በሰዎች የሚሰሩ የተለያዩ ተግባራት አሉ፡፡ ከነዚህም ተግባራት መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፊትን መታጠብ
- ጥርስን መፋቅ
- ወደ ትምህርት ቤት መሄድ
- ቤት ማፅዳት
- መፅሀፍ ማንበብ
- አቅመ ደካሞችን ማገዝ

- የተለያዩ ጨዋታዎችን መጫወት


### ውይይት 1

ከዚህ በታች ከቀረበ ምስል ምን ተረዳችሁ? ተራ በተራ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡




በየዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራት ብዙ ናቸው:: እነዚህም በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ የሚሰሩ ናቸው:: ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ ተመልከቱ::

እነዚህም ተግባራት በአከባቢያችን የሚከናወኑ ስራዎችን የሚያሳዩ ናቸው::

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| ጤፍ መፍጨት | በቆሎ በውቀጥ | ቡና ማፍላት |
|  |  |  |
| ላም ማልባት | ጤፍ ማበጠር | ስፌት መስፋት |

## መልመጃ 1

### ከላይ የቀረቡትን ስዕሎች ከተመለከታችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. በስዕሉ ላይ ከቀረቡት ድርጊቶች ያስገረማችሁ የትኛው ነው? ለምን?
2. በስእሉ ላይ ያያችሁትን ድርጊቶች ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ፡፡
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የዕለት ተዕለት ድርጊቶችን በመስመር ንድፍ አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ 2
# የፈጠራ ችሎታ

## 2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መጻፍ፣ ማንበብና መጫወት

### ተግባር 1

1. ሙሉ ኖታ ያለውን የምት ዋጋ እና ቅርጹን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::
2. ግማሽ ኖታ ያለውን የምት ዋጋ እና ቅርጹን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::


### ተግባር 2


1. ሙሉ ዕረፍት ያለውን ምት እና ቅርጹን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::
2. ግማሽ ዕረፍት ያለውን ምት እና ቅርጹን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ::
3. በቡድን በመሆን የኖታን እና የዕረፍትን ልዩነት ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍሉ ተማሪዎች በቃል ተናገሩ::

### ልምምድ


ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግማሽ ኖታ እና ግማሽ ዕረፍትን ታ... እያላችሁ እጃችሁን እያጨበጨባችሁ ወይም ዴስካችሁን ቀስ ብላችሁ እየመታችሁ

## ተጫወቱ፡፡


1. 

2. 

3. 

4. 

5.




6.




7.



8



9



## 2.2 ውዝዋዜ እና ነጻ እንቅስቃሴ

### የግንዛቤ ጥያቄ

1. ሰዎች ውዝዋዜ ሲያደርጉ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ውዝዋዜውን የሚያደርጉት እንዴት ነው?

ሰዎች ከባህላቸው ጋር የተያያዙ የተለያዩ የውዝዋዜ አይነቶች አላቸው። ውዝዋዜ የተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ይህም ከቦታ ቦታ እንዲሁም እንደባህሉ የሚለያይ ነው። ስለሆነም የተለያዩ የውዝዋዜ አይነቶች አሉ። ለምሳሌ በኦሮሚያ ካሉት የውዝዋዜ አይነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

**ሸጎዬ**



## ትሪ



## ጌሎ




## ረገዳ



## ትርትርሳ እና የመሳሳሉት



### ተግባር

በአከባቢያችሁ ከምታውቋቸው የውዝዋዜ ዓይነቶች አንዱን በመምረጥ በቡድን ተለማመዱ። በመቀጠል ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## 2.3 የተውኔት ጨዋታ ፈጠራ



አእምሮ የተለያዩ ሀሳቦችን ማመንጨት እንደሚቻል



የተውኔት ጨዋታን በመፍጠር ላይ ያሉ ተማሪዎች



የፈጠራ ችሎታ አንድ ሰው አዕምሮን በመጠቀም ሀሳብ በማመንጨት አዲስ ነገር መፍጠር ወይም መስራት ነው።

## ልምምድ 1

በምዕራፍ አንድ ውስጥ የተማራችሁትን የተውኔት ጨዋታ እንደ መነሻ ሀሳብ በመውሰድ ከምታውቋቸው ተረቶች ተውኔት በመፍጠር ተጫወቱ።

## ልምምድ 2

አንድ ሕጻን ጠዋት ከእንቅልፍ ተነስቶ እስከ ማታ የሚያከናወኗቸውን ተግባራት በመጠቀም ተውኔት አዘጋጁ:: ከዚያም በቡድን በመለማመድ ለክፍል ተማሪዎች አቀርቡ::



## ልምምድ 3

በክፍላችሁ ውስጥ ስለሚገኙ ተማሪዎች አነጋገር አለባበስና አካሄድ በማስመሰል ተውኔት በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።






## መልመጃ1

1. የፈጠራ ችሎታ ማለት ምን ማለት ነው?


## ተግባር

የፈጠራ ችሎታን በተመለከተ ከላይ መምህራችሁ ያቀረቡላችሁን ገለጻ እንደ ምሳሌ በመጠቀም የተውኔት ጨዋታን በመፍጠር ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## 2.4 መስመሮችን ማስመርና ቀላል ንድፍ መስራት



መስመር የሚመሰረተው ከነጥቦች ነው:: እነዚህ የተሰመሩ መስመሮች የአንድን ንድፍ ድንበር የሚያመለክቱ ናቸው:: በንድፍ ውስጥ መስመር ትልቅ ድርሻ አለው:: አንድ ቀጥተኛ የሆነን መስመር በትክክል ለማስመር ደጋግሞ መለማመድ አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ እጃችሁን ለማፍታታት ቀጥሎ የቀረቡትን መስመሮች ደጋግማችሁ መለማመድ አለባችሁ:: እጃችሁን በሁሉም አቅጣጫ ደጋግማችሁ በማስመር መለማመድ ይጠበቅባችኋል::




በተለያየ አቅጣጫ ያለጥንቃቄ የተሰመሩ መስመሮች


## 2.4.1 መስመር በመጠቀም ንድፍ መንደፍ




በመስመር ንድፍ መንደፍ ማለት ምንም ነገር ሳይጭምሩበት በመስመር ብቻ የአንድን ነገር ቅርጽ በማንሳት ማሳየት ማለት ነው።

**ምሳሌ 1. ከዚህ ቀጥሎ በመስመር ብቻ የተነደፉ ቅርጾችን ተመልከቱ።**








| | |
|---|---|
|  |  |
|  |  |
|  |  |
|  |  |


## ልምምድ 1

### ቀጥሎ በ 1፣ 2 እና 3 ላይ በጅምር የቀሩትን ንድፎች የተጠናቀቀውን ንድፍ 4ን በመመልከት አሟሉ።




## ልምምድ 2

**ቀጥሎ ከ 1-5 በመስመር ተያይዘው ያላለቁትን የአውሮፕላን ምስሎች በ 6 ላይ ተሟልቶ የቀረበውን በመመልከት በትክክል ንደፉአቸው::**



## ልምምድ 3


**ቀጥሎ ከ 1-11 ሳይጠናቀቅ የቀረበውን የዓሳ ንድፍ የተጠናቀቀውን 12 ን በማየት አጠናቅቁ::**




## ልምምድ 4

**ቀጥሎ ከ1-5 ሳይጠናቀቅ የቀረበውን የመኪና ንድፍ የተጠናቀቀውን 6ን በማየት አጠናቅቁ::**


1




2




3




4



5



6




## ልምምድ 5

1. የሚከተለው ስዕል ምንድን ነው? የስዕሉን ንድፍ ደብተራችሁ ላይ ንደፉ።




## ልምምድ 6

1. የሚከተለውን ስዕል በደብተራችሁ ላይ ንደፉ።



## ልምምድ 7

1. የሚከተለውን ንድፍ አስመስላችሁ በደብተራችሁ ላይ ንደፉ።




# ልምምድ 8

1. በ ሀ ስር ያለውን ስዕል በመመልከት ለ ስር ያለውን ንድፉን በማስቀመጥ ሀ ስር በተቀበው መሠረት ቀለም ቀቡ፡፡

"ሀ" "ለ"



# ምዕራፍ 3

# የታሪክ እና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ

## 3.1 ባህላዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ

### የአመት በዓል መዝሙር/ዘፈን

የግንዛቤ ጥያቄዎች


1. በዓመት በዓል ወቅት ምን ምን አይነት ዘፈኖች ይዘፈናሉ?

2. የምታስታውሱትን ሶስት ዘፈኖች በጋራ ከተለማመዳችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

ቀጥሎ በበዓላት ቀናት የሚዘፈኑ ዘፈኖች ግጥም እንደ ምሳሌ በጽሑፍ ቀርቦላችኋል:: ግጥሙን እያነበባችሁ በውዝዋዜ መልክ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

### የአዲስ ዓመት ዘፈን

አውራጅ ተቀባይ



እዮኮ ደራር ............እዮኮ ደራር 2x

1. በብሳ ጉብኔ...እዮኮ ደራር

በረ ኢፋ ጎዲ ደራር.. እዮኮ ደራር

ብየ ናጋ ጎዲ ደራር..      እዮኮ ደራር

መሸጋገሪያ.......

2. ብራ ሞቲ አያና ...        እዮኮ ደራር

ብራ ማልቱ ወላላ ደራር..      እዮኮ ደራር

ብራ ማልቱ ጫላ ደራር.... እዮኮ ደራር መሸጋገሪያ......

3. ኢብሳን ኢፋ ደራር...      እዮኮ ደራር

ብራን በርኤ ደራር... እዮኮ ደራር

አባቦን ደራሬ ደራር..      እዮኮ ደራር


መሸጋገሪያ.....

4. በር ኒደርባ ደራር.. እዮኮ ደራር

ኦፍ እንቱሊን ደራር ... እዮኮ ደራር

ጉዳን ዋቃ ደራር ...እዮኮ ደራር

መሸጋገሪያ.......



## የእንስሳት ሙገሳ መዝሙር

ሰዎች ከሚጠቀሙባቸው ባህላዊ መዝሙሮች አንዱ የእንስሳት ሙገሣ መዝሙር ነው:: ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ በቡድን ከተለማመዳችሁ በኋላ ዘምሩ::


# የእንስሳት ሙገሳ መዝሙር




ማል ወያ ማል ወያ
ሎን ወያ ሎን ወያ
ዱጉማ ሎን ወያ
ሳወነወ ጀሩ ጃርሳ



ጅሩ ደርገጌሳ
ዱጉማ ሎን ወያ
ድበት በሬዳ
ዱገን ቀበኔሳ
ቀዬ ሳዊ ጅሩ
አገዲንሳ መርጋዳ



ቡሊትንሳ መረራዳ
ኬሱማን ኡልፎዳ
ዱጉማ ሎን ወያ
ሳወን ጋፊ ፊኩ
ዮ ሲደበን ሀንቁ



# 3. 2 ተረት

## አኮማኖዬ

በቀድሞ ዘመን "አኮማኖዬ" የሚትባል ንግስት ነበረች ይባላል። ንግስትነቷን በመጠቀም ብዙ የሚገራርሙ ነገሮችን ትሰራ ነበር። አኮማኖዬ በንግስናዋ ዘመን የሚከተሉትን ውሳኔዎች በምታስተዳድራቸው ሕዝብ ላይ በቅደም ተከተል ታስተላልፍ ነበር።



ውሳኔዎቿንም አጫጭር ሰዎች ብልሆች ስለሆኑ ትዕዛዟን ስራ ላይ ስለማያውሉ እና ስለሚቃወሙኝ ከምድረገጽ አጥፉልኝ በማለት ጀመረች።



አጭር ሽማግሌ ፍለጋ የሚሄዱ ሰዎች



አጭሩ ሽማግሌ፡ እስቲ ለሆነ ነገር ስለምጠቅማችሁ ጉድጓድ ደብቁኝና አስቀሩኝ፡፡



ሰዎች፡ እሽ አንድ ቀን እኛንም ትጠቅም ይሆናል በማለት ደብቀው አስቀሩት።

ሰዎች፡ ንግስታችን ሁሉንም አጫጭር ሽማግሌዎችን ገድለን መጥተናል።



አሁን በመሬትና በሰማይ መካከል ቤት ስሩልኝ አለቻቸው።

ሰዎቹም አንድ ላይ ተመለሱና የደበቅነው ሽማግሌ ዘንድ መሄድ አለብን ከእርሱ መፍትሔ እናገኛለን ብለው ተስማሙ፡፡



አጭሩ ሽማግሌ፡ እንደምትሏት፣ እኛ ቤቱን እንሠራለን ነገር ግን የቤቱን ምሳሶ የሚያቆመው ባለቤቱ ስለሆነ አንቺ ምሳሶውን ታቆሚያለሽ በሉዋት፡፡

ሰዎቹም ወደ አኮማኖዬ ተመለሱና እኛ ቤቱን እንሠራለን ነገር ግን ምሳሶ የሚያቆመው ባለቤቱ ስለሆነ አንቺ ምሳሶውን አቁሚ አሉዋት፡፡



የቀረ አጭር ሽማግሌ አለ ማለት ነው፤ እንደዚያ ከሆነ ይህንን ቤቴን ከዚህ ሳታንቀሳቅሱ በሩን ወደ ተራራ አዙሩና አውጡልኝ አለች፡፡




ሰዎች፡ አሁንም መፍቴሔ ካንተው እንፈልጋለን፡፡ አኮማኖዬ ቤቴን ሰታንቀሳቅሱ በሩን ወደ ሰማይ አዙሩና አውጡልኝ ብላለች፡፡ ምን ይሻለናል?



አጭሩ ሽማግሌ፡ እሷ ከተኛች የመጀመሪያውን በር ዝጉና ሌላ በር ወደ ተራራ አዙራችሁ አውጡላት።

ምን እንደማዛችሁ የማጣ መሰላችሁ! በፍጥነት ከፈረስ በታች ከአህያ በላይ የሆነ ነገር አምጡና ላዩ ላይ አስቀምጡኝ።



ሰዎች፡ እሺ

ከዚያ የሜዳ አህያ አመጡና ላዩ ላይ አስቀምጧት በላዩ ላይ

አሰሩዋትና ለቀቁዋት፡፡



ከዚያ በኋላ የሜዳ አህያ አኮማኖዬን ይዛ ሄዳ ገደል

ከተተቻት፡፡ አኮማኖዬን እዛው አስቀረቻት፡፡



## መልመጃ

1. ከዚህ ተረት ውስጥ ያስደሰታችሁ ነገር ምንድን ነው?

2. ከአኮማኖዬ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

# 3.3 የአካባቢ ቀለማት

## ተግባር 1

1. በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ቀለማት በትኩረት ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ ሳር፣ የቦቆሎ፣የስንዴ፣ የግራዋ እና የብሳና ቅጠሎች ምን ዓይነት ቀለም አላቸው?

2. ከዚህ በታች ያለው ስዕል ምን ዓይነት ቀለም አለው? ተናገሩ።



ቀለም ማለት የአንድ ነገር ገጽታ ነው። የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ፍላጎቱንና ምኞቱን ከሚገልጽባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ቀለም ነው። ስለዚህ ቀለማትን በመጠቀም ቤትን፣ ልብስን እና የመሳሰሉትን ማሳመርና ማደስን ያከናውናሉ። ለምሳሌ በፀደይ ወቅት የአደይ አባባና ሣር ይዘው እሬቻ ይሄዳሉ።




ስለዚህ የአካባቢ ቀለማት ማለት በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች መልክ ማለት ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለያዩ የኦሮሚያ አከባቢዎች የተለያዩ ስነስርዓቶችን ለማክበር የባህል ልበሶችን፣ ባህላዊ የምግብ ዕቃዎችን፣ መጠጥ የሚቀርብባቸው ዕቃዎችና የመሳሰሉትን ይዘው በስነስርዓቱ ላይ ይገኛሉ።

## ለምሳሌ፡



በእሬቻ በዓል ላይ ሰዎች የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ልብሶች ለብሰው ሲሄዱ

በአጠቃላይ የኦሮሞ ህዝቦች የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የባህል ዕቃዎችና ልብሶችን ለተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከተለው ይጠቀሙበታል፡፡





## የተለያየ ቀለም ያላቸው የባህል ልብሶች



## የተለያየ ቀለም ያላቸው ባህላዊ እቃዎች

## መልመጃ 1

1. በሚከተለው ሰንደቅ አላማ ላይ የሚገኙ ቀለማትን ፃፉ::



ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

2. በአከባቢያችሁ የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳት ያላቸውን ቀለማት ፃፉ

ሀ. ____________________


ለ. ____________________

ሐ. ____________________

መ. ____________________

## ልምምድ 1

ቀጥሎ የቀረበውን የኦዳ ምስል በደብተራችሁ ላይ ንደፉ:: ከዚያም አረንጓዴ ቀለም በመቀባት ኦዳ እንዲመስል አድርጉ::



# 3.4 ባህላዊ ድራማ

ባህላዊ ድራማ ሙሉ በሙሉ በኅብረተሰቡ ባህል ላይ ተመስርቶ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተዘጋጅቶ ባህሉን ብቻ እንዲያንጸባርቅ ተደርጎ የሚቀርብ ድራማ ነው።

ከዚህ በመቀጠል በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ከሚታወቁ ስነስርዓቶች መካከል "ጅላ ጉብሳ" በባህላዊ ድራማ መልክ ቀርቦላችኋል።

የ"ጅላ ጉብሳ" ስነስርዓት ለደበሌ ስም ማውጣትን የሚያመለክት ነው።ይህ ጉባኤ አንድ ልጅ ከደበሌ የዕድገት ደረጃ ወደ ትናንሽ ጋሜ ሲሸጋገር የሚከናወን ነው።

## የ"ጅላ ጉብሳ" ጨዋታ

ደበሌዎች የደበሌን መዝሙር ሲዘምሩ ክብ ሰርተው ይጫወታሉ።



አውራጅ ተቀባይ

ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ--- ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ-- ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

ደባሉምኒማሬ ኦልቻን ስልጋ..ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

ከናን ሲደብሬ ላሶ ኦልቻን ስልጋ...ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

ኪቾላ ጋዳን እትገልቴ ኦለቻን ስልጋ ... ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

አነኪን ጉደቴ ኦልቻን ስልጋ ... ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

አባ ጋዳ- አዳራሽ ተገንብቶ ተጠናቋል



ደበሌን ወደ አዳራሹ አስገቡት

ቁንጮውን ላጭተን ስም እንሰይመዋለን



ደበሌዎች ይጮሃሉ፡ ቁንጮአችንን ልትላጩብን ነው ወይ?

ቁንጮዬ ቁንጮዬ

የደበሌነቴ ምልክት

የቅምጥልነቴ ምንጭ

ደህና ሁን ቅጽል ስሜ

ቁንጮዬ ወደ ጋሜ ልቀየር ነው

እንኳን ደህና መጣህ የስሜ ስያሜ

**ወይዘሮ ሎኮ፡** ያችን የስጦታ ጊደር ከሜዳ ላይ አምጡና

በር ፊት ጠብቁን፡፡



አውራጅ ተቀባይ

ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ .... ደበሌ ለሶ ኦልቻን ስልጋ

ማፍ እንዳወኔ ዳላቱ .... ማፍ እንዳወኔ

ኪቻላ ............................ ማፍ እንዳወኔ

መልቀቃ.......................... ማፍ እንዳወኔ

ደበሌ ........................ ማፍ እንዳወኔ

**ወይዜሮ ሎኮ፡** በባህሉ መሰረት የሚያስፈልገውን ነገር አቅርበናልና አሁን መጥታችሁ ስጦታችሁን ከበሩ ላይ ውሰዱ አለች፡፡



ከዚያም ልጆች እየዘመሩ ይወጣሉ

ቁንጮዬ ቁንጮዬ

የደበሌነቴ ምልክት

የቅምጥልነቴ ምንጭ

ደህና ሁን ቅጽል ስሜ





## መልመጃ 2

1. ሙሉ በሙሉ በኅብረተሰቡ ባህል ላይ በማተኮር ባህሉን በፈጠራ ቃላት አሳምሮ የሚያቀርብ ድራማ ዓይነት ------------ይባላል።

## መልመጃ 3

1.ከላይ በቀረበላችሁ ባህላዊ ድራማ መሰረት በአከባቢያችሁ በሕጻናት ጉዳይ ላይ ስለሚከናወኑ ድርጊቶች ቤተሰባችሁን በመጠየቅ ለመምህራችሁ ንገሩ።

# ምዕራፍ 4
# የስነጥበባት ማራኪነት

## 4. የስነ-ጥበብ ድርጊቶችን ማድነቅ

### 4.1. ሙዚቃን ማድነቅ

#### ተግባር 1

1. በአከባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ ሙዚቃዎች ምን ምን ናቸው? ከምታውቋቸው ውስጥ የተወሰኑትን ተራ በተራ ለቡድን ተማሪዎች አቅርቡ።
2. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ባህላዊ ሙዚቃዎች የበለጠ ያስደሰታችሁ የትኛው እንደ ሆነ ከምክንያቱ ጋር ግለፁ።

የኦሮሞ ህዝብ በዕለት ተዕለት ኑሮው ውስጥ የሚያደንቃቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ሙዚቃ አንዱ ነው። ምክንያቱም

- በሙዚቃ ባህሉንና ታሪኩን ይገልፃል።
- ጀግንነቱን ያንፀባርቅበታል።
- እምነቱን ያካሄድበታል።
- በልማት ውስጥ ለመበረታቻ ይጠቀምበታል።
- ትምህርት ይማማሩበታል።
- ይዝናኑበታል ወዘተ።

# 4.2. የስነጥበብ ስራዎች ማድነቅ

## ውይይት 1

የስነ-ጥበብ ስራዎች የሚገኙበትን ቦታ ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ? ጎብኝታችሁ ከሆነ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው?

የስነ-ጥበብ ስራዎችን ማድነቅ ማለት የተለያዩ የስነ-ጥበብ ስራዎችን አሰራራቸውንና ከምን እንደተሠሩ መመልከትና አድናቆትን መግለፅ ነው።

### 4.2.1. የስነ-ጥበብ ስራዎችን መጎብኘት

የስነ-ጥበብ ስራዎችን መጎብኘት የአድናቆት ስሜትና አንድን ነገር የመፍጠር ክሂልን ያዳብራል።

#### ሀ. የስነጥበብ ማሳያ ቦታ

የስነጥበብ ማሳያ ቦታ ማለት የስነ-ጥበብ ውጤቶችን በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ለእይታ የሚያቀርብበት ቦታን የሚያመለክት ነው። የስነ-ጥበብ ስራዎች ማሳያ ቦታ ሄደው ከተመለከቱ ለስነጥበብ ያላቸው አመለካከት ከፍ ይላል። ይህም አንድን ነገር የማድነቅ ስሜት፣ ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታ፣ የተነሳሽነት መንፈስ እና የመሳሰሉትን እንድያሳድጉ ያግዛቸዋል።

በአጠቃላይ ይህ የማድነቅ ስሜት፣ የምስሉን መልዕክት፣ መስመሮች፣ ቅርፅ፣ ቀለማትንና ለስነ-ጥበብ ያላቸውን አመለካከት ያሳድግላቸዋል፡፡









የክብር ዶክተር አርቲስት ለማ ጉያ የስነ-ጥበብ ስራዎች

## ለ. ሙዚየም መጎብኘት

ሙዚየም ጥንታዊ የታሪክ እና የባህል ቅሪቶች ተሰብስበው የሚቀመጡበት ቦታ ነው። ሙዚየም የአንድን ሀገር ዘመናትን ያስቆጠሩ አስደናቂ እና ስለጣኔን የሚያሳዩ ብዙ ነገሮች የሚገኙበት ነው።

ስለዚህ የአንድን ማኅበረሰብ ጥንታዊ ስልጣኔ ለማወቅ ሙዚየም ውስጥ የታሪክ እና የባህል ቅሪቶች መኖራቸው ወሳኝ ድርሻ አለው።

ሙዚየሞችን መጎብኘት ያለው ጥቅም ያለንን ጥንታዊ የሆኑ የታሪክ ቅሬታዎቻችንን ማወቅ እና ማድነቅ እንዲሁም ትምህርት መቅሰም ነው። ይህም ተማሪዎች ባህላቸውን አውቀው እንዲንከባከቡ እና የሀገራቸውና የሕዝባቸው ስልጣኔ ምን እንደሚመስል የሚማሩበት ቦታ ነው።


OROMO CULTURAL CENTER
GERETTA




## ሐ ስዕላዊ መግለጫ

ስዕላዊ መግለጫ የአንድን አካባቢ ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በፅሁፍ በተደገፈ ስዕል በቀላሉ መግለጽን የሚያመለክት ነው። ይህም ትምህርት ወይም መልዕክት ለማስተላለፍ ይረዳል። አንድ ጽሑፍ በስዕል ተደግፎ ከቀረበ መልዕክትን በቀላሉ ለማስተላለፍ እንደሚያግዝ የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ አንድን ጽሑፍ በስዕል አስደግፈን ካቀረብን ጽሑፉን ብቻ አንብበን መረዳት ያልቻልነውን ስዕሉን በማየት በቀላሉ እንድንረዳ ያግዘናል ማለት ነው።

ስለዚህ ይህ ከጽሑፍ ጋር የቀረበ ስዕል ስዕላዊ መግለጫ ይባላል። አንድን ስዕል ብቻ በመመልከት ጽሑፉን ሳናነብ የሚያስተላልፈውን መልዕክት መረዳት ይቻላል። እንዲሁም ልጆች ስዕላዊ መግለጫን የመረዳት እና የመተርጎም ችሎታ እንዲያዳብሩ ያደርጋል። ለምሳሌ

በድሮ ዘመን አንበሳ፣ ጅብ እና ቀበሮ ሆነው መንገድ ሲሄዱ ነበር፡፡



ሩቅ መንገድ ከመሄዳቸው የተነሳ ስለደከሙ ለማረፍ አንድ ዛፍ ስር ተቀመጡ፡፡



ቁጭ ብለው ግራ ቀኛቸውን ሲመለከቱ በሬ፣ ግመል እና ፍየል አገኙ፡፡ ከዚያም አንበሳ በጣም ደስ ብሎት እስቲ አከፋፍሉልን አላቸው፡፡ ጅብ ሆዳም ስለሆነ በችኮላ እኔ አከፋፍላለው አለ፡፡



እሱም ግመል የአንበሳ ነው፤ በሬ የእኔ ይሁን፡፡ ፍዬል ደግሞ ለቀበሮ ይሰጥ አለ፡፡ ከዚያም አንበሳ በጣም ተበሳጭቶ ጅቡን መትቶ ገደለው፡፡



በመቀጠል ለቀበሮ እስቲ አንተ ደግሞ ለሁለታችን አከፋፍልልን ብሎ ጠየቀው::

ቀበሮም ተመቶ ከሞተው ጅብ በመማር ፍየል ለቁርስህ ትሆናለች፣ በሬው ደግሞ ለምሳህ ሲሆን ግመል ደግሞ እራትህ ትሆናለች ብሎ መለሰለት:: አንበሳውም ደስ ብሎት እንዲህ በጥሩ ሁኔታ መከፋፈልን ማን አስተማረህ? ብሎ ጠየቀው:: ቀበሮም እራሱን ተመቶ ከሞተው ከዚህ ከሞተ ጅብ ነው የተማርኩት ብሎ መለሰለት ይባላል::



## መልመጃ 1.

የሚከተሉትን ጥያቄች በቃል መልሱ።

1. በታሪኩ ውስጥ ከቀረቡት ማንን ታደንቃላችሁ?
2. ከዚህ ስዕላዊ መግለጫ ምን ተማራችሁ?

# 4.2.2. ነፃ ንድፍ

**ተግባር 2**


1. በእርሳስ ንድፍ ሰርታችሁ ታውቃላችሁ? አንዴት እንደሰራችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የባህላዊ ዕቃዎችን ንድፍ በእርሳስ ደብተራችሁ ላይ ስሩ፡፡

ነፃ ንድፍ ማለት በአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ማለትም እርሳስ፣ ጭላሽት፣ ኪራዮንና ወረቀት በመጠቀም ንድፍ መስራት ማለት ነው፡፡

**ልምምድ1**

የሚከተሉትን እቃዎች በማየት ንደፉ፡፡

1. ከለቻ



## 2. ሖሮሮ



Rectangular Snip

## 3. ሲንቄ



# 4.3 የተውኔት ጨዋታ

**የኦሮሞ ሕዝብ አኗኗር በስነ-ጥበብ የተሞላ ነው:: በእያንዳዱ የሕጻናት የዕድገት ደረጃ ውስጥ ባህልን ጥበብ በተሞላበት አኳን በሕጻናት ውስጥ ይቀርጻሉ:: በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ ማራኪ በሆነ ንግግር የፈለጉትን መልዕክት ያስተላልፋሉ::**

*ሀራራን ጫንጫጻሊሳ*



**ይህ ጨዋታ በግጥም መልክ የሚቀርብ ሲሆን እየተቀባበሉ የሚጫወቱት ነው::**

*ሀራራን ጫንጫጻሊሳ    ሀ ሀ ሀ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ*

ሀራራን ጫንጫጻሊሳ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ድቆ ትያ ጉዶ ትያ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ቦሩ አቺ ዴምቲ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ሞቃ ቀበቴ ዴምቲ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ዋን ኛቱ ደብዴ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ቆሪ ቢያ አርካ ኬቲ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

እሲን ጋድ እንተሱ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ታ ብያ ከጄልቲ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ዋን ኦፊ እንዳበቱ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

መና ቢያ ጃላ ዴምቲ ሀራራን ጫንጫጻሊሳ

ሴቶች መሃል በመግባት ከራሳቸሁ ይከላከላሉ፡፡



ሆ... ሆ ዮ ዮ... ሆ... ሆ ዮ ዮ...

ሆ... ሆ ዮ ዮ...        ሆ... ሆ ዮ ዮ...

ዮም መና ናፍ ጃርቴ

ሆ... ሆ ዮ ዮ...        ሆ... ሆ ዮ ዮ...

ናኮማቹፍ ካቴ

ሆ... ሆ ዮ ዮ...        ሆ... ሆ ዮ ዮ...

አት አሳ ኦልቴ

ሆ... ሆ ዮ ዮ...        ሆ... ሆ ዮ ዮ...

ዋን መና ዮም ጋርቴ

ሆ... ሆ ዮ ዮ...        ሆ... ሆ ዮ ዮ...



አት አካኬ ህንቤክቱ        አራራን ጫንጫጳሊሳ

አካ ካንኬ ናት ስትህማ        አራራን ጫንጫጳሊሳ

ካኦፊ ኛቴ ህንዱግዱ        አራራን ጫንጫጳሊሳ

ከብያ ጃላ ቡልቲ አራራን ጫንጫጻሊሳ

አቲ ከብያ ማኛታ አራራን ጫንጫጻሊሳ

ከንኬ ፊጤ አቺ ፊግዳ አራራን ጫንጫጻሊሳ

አት ሲ መና ህንቃብዱ አራራን ጫንጫጻሊሳ

መና ከንኬ ዲስቴ አራራን ጫንጫጻሊሳ

ከን ኦላ ከጄልታ አራራን ጫንጫጻሊሳ

## መልመጃ 1

1. የአራራን ጫንጫጻሊሳ ጨዋታ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?
2. በዚህ ጨዋታ ውስጥ ያስደነቃችሁን ከክፍል ተማሪዎች ጋር ተወያዩ፡፡

# ምዕራፍ 5

# የስነጥበባት ግንኙነት

## 5.1. በስነ-ጥበባት መካከል ያለ ግንኙነት

ስነ-ጥበባት ስዕል፣ ሙዚቃ፣ ተውኔት፣ ውዝዋዜ እና የፊልም ስራዎችን ያጠቃልላል። የሰውልጅም እነዚህን ጥበባት በመጠቀም በውስጡ የተቀመጡትን እምቅ ችሎታ ይገልጥበታል።

### ተግባር

1. ከትራፊክ አደጋ ራሳችንን እንዴት መታደግ እንደምንችል ሙዚቃን፣ ስነጥበብን እና ተውኔትን በማዘጋጀት በቡድን ተከፋፍላችሁ በሙዚቃ፣ በስዕል እና በድራማ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።
2. የማሲንቆ፣ የክራርና የከበሮ ስዕል ከነደፋችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ።

## 5.1.1. የሙዚቃ ተግባራት

### የግንዛቤ ጥያቄ

1. ሙዚቃ ከምን ምን ጋር ግንኙነት አለው?

የሚከተሉትን መዝሙሮች ግጥሙን ከአነበባችሁ በኋላ ዘምሩ።

### የቀለማት መዝሙር



ቀለማትን እንወዳለን
በቀለማት ደስታ እናገኛለን
አረንጓዴና ቀይ
ደግሞም መሳይ ሰማያይ
ጥቁር ነጭ ቢጫ
ቡናማ ግራጫ
አከባቢያችንን ንረዳበታለን
ባይኖቻችን አይተን ደስታ ናገኛለን

አረንጓዴ ቀለም

አንቺ ነሽ ለምለም

ሰማያዊ ቀለም

እንደንቺ ሳቢ የለም

ቀይ ቀለም ደግሞ

ይጣራል ከሩቅ

ይሄ ነው ተግባሩ

ሁሉንም ማድመቅ



## የሙዚቃ ትምህርት መዝሙር

ሙዚቃ እንማራለን

ድስታ እናገኛለን

ባነድነት እየዘመርን

እንዝናናበታለን

አእምሮን ያድሳል
ትምህርትም ይሰጣል
ባህል ለማሳደግ
በብርቱ ይጠቅማል
እኛም በሙዚቃ ሁሌ እንማራለን
ባህል ወጋችንን እናሳድጋለን 2x

## የሙዚቃ እና የባህል መሳሪያዎች መዝሙር



ሙዚቃ መልካም ነው
የአለም ቋንቋ ነው
ያንዱን ባህል ላንዱ
ማስተላለፊያ ነው
መስንቆ እና ክራርን
ከበሮ ደለቅን
ባህል ወጋችንን እናሳውቃለን።

# 5.2. ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር የስነጥበባት አስፈላጊነት

## 5.2.1. ተውኔት በተመለከተ

### የግል ንጽህና

መምህራን በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ጊዜ ስለ የግል ንጽህና ሲያስተምሩ ተማሪዎች የሚና ጨዋታን በመጫወት በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ ይችላሉ::



ለምሳሌ: ተማሪዎች የተማሪዎችን፣ የጓደኞቻቸውን፣ የቤተሰብን እና የጤና ባለሙያዎችን ሚና ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች እንደ መነሻ በመጠቀም አጫጭር ጨዋታዎችን ተጫወቱ::

አንድ ወንድ ተማሪ በጠና ስለታመመ ጓደኞቹ ከትምህርት ቤት ይዘው ወደ እናቱ ቤት ወሰዱት።



እናቱም ልጃቸው በጓደኞቹ ታዝሎ ስመጣ አይተው በጣም ደነገጡ።

**እናት**: ልጄ ምን ሆነ?



**ከጓደኞቹ አንዱ፡** የኢብሳ እናት ... ልጆት ሁልጊዜ እጁን ሳይታጠብ ነው የሚበላው። መጸዳጃ ቤት ገብቶ እንደወጣ እጁን ሳይታጠብ ምግቡን ይበላል።

**እናት፡** ልክ ነው ልጄ እኔም ደጋግሜ ነግሬዋለሁ...ይህንን ምን አባቴ ባረገው ይሻላል! እባካችሁ አሁን ፈጥነን ወደ ሐኪም ቤት እንውሰደው!

ወደ ሐኪም ቤት ከወሰዱ በኋላ ...

**እናት:** እባካችሁ ልጄ በጣም ስለታመመብኝ ቶሎ ድረሱልኝ!

**ኢብሳ:** ወይኔ እናቴ ሆዴን እየቆረጠኝ ነው ኡ..ኡ..ኡ አ...።



ዶክተሯ መጥታ ቶልቶሎ ምርመራ አደረገችለት።



እናት: በሽታው ምንድንነው?

ዶክተር: የግል ንጽህና ከአለመጠበቅ የመጣ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ጥቂት ቆይቶ ቢሆን ኖሮ ለሕይወቱም ያሰጋ ነበር። አሁን ቶሎ ብለህ ይህችን መደሀኒት ዋጥ።

ከዚህ በኋላ የግል ንጽህናህን በደንብ መጠበቅ ይኖርብሀል። እንዲሁም እጅህን ሳትታጠብ ምግብ እንዳትመገብ!

ኢብሳ: እሺ



## መልመጃ 1

1. ከዚህ አጭር ጭውውት ምን እንድተማራችሁ ለክፍል ተማሪዎች በቃል ተናገሩ።

## 5. 2. 2· ሙዚቃን በተመለከተ

እንደ ተውኔት ሁሉ ሙዚቃም ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ለማስተማር ወሳኝ ድርሻ አለሁ።

ይህም ትምህርቱን በመዝሙር መልክ በማቅረብ ሳቢ ለማድረግ ይረዳል። ለምሳሌ ፡

1· የእንግሊዝኛ ፊደላትን በመዝሙር በቀላሉ መማር ይችላሉ።


2· ስለ ግል ንጽህና መጠበቅ በተመለከተ በመዝሙር መማር ይችላሉ።

## 5. 2. 3. ስነጥበብን በተመለከተ

### ውይይት 1

**ስነ-ጥበብን በመጠቀም ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን እንዴት መማር እንደሚቻል ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ::**

**ስነጥበብን በመጠቀም ቋንቋን መማር እንደሚቻል ቀጥሎ ከቀረበ ስዕል ተመልከቱ::**



ልጆች ቋንቋን መማር የሚጀምሩት መጀመርያ ከወላጆቻቸው/ ከአሳዳጊዎች እና ከአከባቢው ኅብረተሰብ ነው::


ከወላጆቻቸው የሚማሩት የንግግር ክህሎትን ሲሆን ማንበብን እና መጻፍን ደግሞ መማር አለባቸሁ::

ለምሳሌ:

ከላይ የቀረበ ምስል አንድ ነገር የት እንዳለ በቀላሉ ለመለየት ያግዛል:: ይህም የሚያሳየው አንድን ጽንስሀሳብ በቀላሉ ለመረዳት ስዕል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያሳያል::

## ፊደላትን በማስተማር ሂደት ውስጥ ስነጥበብ ያለው ፋይዳ

ተማሪዎች የፊደላትን ቅርጽ ከሚያውቁት ነገር በመስራት ከተማሩ የፊደላቱን ቅርጽ በቀላሉ እንዲያውቁ ለማድረግ ይረዳቸዋል።



ከእንጨት የፊደላትን ስዕል መቅረጽ

ለምሳሌ፡

ሀ- ይህ ፊደል ከሁለት ቋሚ መስመሮች እና ከአንድ አግድም መስመር ይመሰረታል።

ለ- ሁለት ሰያፍ መሰመሮችን በማገናኘት ይመሰረታል።

መ- ደግሞ ሁለት ክብ እና አንድ አግድም መስመሮችን በማገናኘት ይመሰረታል።


እነዚህን ፊደላት በማገናኘት ቃል መመስረት ይቻላል።

ለምሳሌ፡ ለመለመ

ስለዚህ መስመሮችን በመጠቀም የተለያዩ ፊደላትን በመቅረጽ የስዕል ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ።

## ስነጥበብ ሕጻናት ሂሳብን በመማር ሂደት ውስጥ ያለው ፋይዳ

ተማሪዎችን ስለ ሂሳብ ስሌቶች ስናስተምር በተለያዩ ምስሎች በመጠቀም በቀላሉ መደመርን እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል:: ለምሳሌ 1+2=3 ብለን ከማስተማር ይልቅ የዶሮዎችን፣ የእንቁላሎችን እና የሙዝን ምስል በማሳዬት ማስተማር ይቀላል::





## ሂሳብን ለማስተማር የሚያገለግሉ ስዕሎች

በዚህም መሰረት ቁጥሮችን ስንደምር ቁጥር ሲጨምር የሚንጠቀመው ምስሎችም እየጨመረ ይሄዳል::

